Helsedirektoratet

# በጤና አገልግሎት ውስጥ ላሉ ታካሚዎች አስተርጓሚ

- በቋንቋዎ መረጃ የማግኘት መብት

---

IS-1976

Tolk for deg som er pasient i helsetjenesten
Språk: Amharisk

ትክክለኛውን እርዳታ እና ህክምና እንዲያገኙ ጥሩ መረጃ እና ውይይት አስፈላጊ ነው። እንደ ታካሚ ለእርስዎ የሚስማማ መረጃ ማግኘት አለብዎት። ስለ ጤናዎ፣ ህመምዎ እና ህክምናዎ ከጤና ባለሙያዎች ጋር መነጋገርዎ አስፈላጊ ነው።

የአስተርጓሚዎች ህግ (2022) እንደሚለው የህዝብ አገልግሎቶች ትክክለኛውን ህክምና ለማግኘት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቁ አስተርጓሚዎችን መጠቀም አለባቸው። እንደ ነርሶች፣ዶክተሮች፣ሳይኮሎጂስቶች፣ወዘተ ያሉ የጤና ሙያተኞች እርስዎ እንደ ታካሚ የሚፈልጉትን እርዳታ እንዲያገኙ የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው።

- እርስዎ በሚረዱት ቋንቋ ስለራስዎ ጤና እና ህክምና መረጃ ሊኖርዎት ይገባል።
- የሕክምና ቃላትን እና አገላለጾችን ለመረዳት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም ትንሽ ኖርዌጂኛ ቢናገሩም አስተርጓሚ ሊያስፈልጎ ይችላል።
- አስተርጓሚው እርስዎ እና የጤና ባለሙያው ባለበት ክፍል ውስጥ ሆኖ ወይም በስልክ ወይም በቪዲዮ መሳተፍ ይችላል።

## የጤና አገልግሎት ሰጪው አስተርጓሚ ማዘዝ አለበት

- የጤና አገልግሎት ሰጪው ተቋም ታካሚው አስተርጓሚ እንደሚያስፈልገው የማጣራት ግዴታ አለበት። ሲያስፈልግ አስተርጓሚ የማዘዝ ግዴታ አለበት።
- እንደ በሽተኛ የትርጉም አገልግሎት በነፃ ያገኛሉ።
- በጥርስ ሀኪም ቤት እርስዎ እንደ አዋቂ ለአስተርጓሚ እና የጥርስ ህክምና ወጪውን እራስዎ መክፈል አለቦት።

## ብቁ የሆኑ አስተርጓሚዎች ብቻ መተርጎም አለባቸው

- ብቁ የሆነ አስተርጓሚ መደበኛ የመተርጎም ብቃት አለው
- ልጆችን እንደ አስተርጓሚ መጠቀም የለብዎትም
- ቤተሰብ፣ ጓደኞች ወይም የሚያውቁትን ማንኛውም ሰው እንደ አስተርጓሚ መጠቀም የለብዎትም

## የተተረጎመ ውይይት እንዲገባዎ ምን ማድረግ አለብዎት?

- የትኛውን ቋንቋ እና የንግግር አይነት/ዘይቤ መናገር እንደሚመርጡ ለጤና አገልግሎት ሰጪው ተቋም ያሳውቁ
- ብዙ ቋንቋዎችን በደምብ አቀላጥፈው የሚናገሩ ከሆነም ያሳውቁ
- ልዩ ፍላጎቶች ካሎት ያሳውቁ፣ ለምሳሌ የመስማት ችሎታዎ ደካማ ከሆነ
- ለውይይቱ በደንብ ይዘጋጁ። ለመጠየቅ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ጥያቄ ጽፈው ያዘጋጁ
- ሁሉም ጥያቄዎች ለአስተርጓሚው ሳይሆን ለጤና ባለሙያው ነው መቅረብ ያለባቸው
- አስተርጓሚውን ካልተረዱት ያሳውቁ
- አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን ይጠቀሙ እናም በግልጽ ይናገሩ። ምክኒያቱም የተናገሩትን ነገር በትክክል ለመተርጎም ለአስተርጓሚው ይቀለዋል
- አስተርጓሚው የተነገረውን ብቻ መተርጎም አለበት። አስተርጓሚው ቀደም ሲል በንግግሩ ውስጥ የተነገረውን መድገም የለበትም
- የተነገረውን እንዲያስታውሱ ማስታወሻ መያዝ ይችላሉ
- አስተርጓሚው በስልክ፣ በቪዲዮ ሲሳተፍ ድምጹ ወይም ምስሉ ጥራት ከሌለው ያሳውቁ

## አስተርጓሚ ምንድን ነው? የአስተርጓሚው ተግባራት ምንድን ናቸው?

- ውይይቱ ሲጀመር አስተርጓሚው በሁለቱም ቋንቋዎች የአስተርጓሚውን ሚና መናገር አለበት
- አስተርጓሚው ገለልተኛ ነው። ይህ ማለት አስተርጓሚው የራሱን አመለካከት ወይም አስተያየት በትርጉሙ ላይ ተጽእኖ ማድረግ የለበትም ማለት ነው
- አስተርጓሚው ሚስጥርን የመጠበቅ ግዴታ አለበት። ሚስጥርን የመጠበቅ ግዴታን መጣስ ወንጀል ነው። ይህ ማለት አስተርጓሚው በንግግሩ ወቅት የተነገረውን ለማንም መናገር አይችልም። ይህ አስተርጓሚው ሥራውን ከለቀቀ በኋላም ይሠራል
- አስተርጓሚው ምክር ሊሰጥ ወይም ለጥያቄዎች መልስ ሊሰጥ አይገባም። አስተርጓሚው መተርጎም ብቻ ነው ያለበት እናም ለታካሚም ሆነ አስጤና ባለሙያተኛ ሰራተኛ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን የለበትም
- ተርጓሚው ያልተረዳው ነገር ካለ ጥያቄዎችን ሊጠይቅ ወይም የተናገሩትን እንደገና እንዲደግሙት ሊጠይቅዎት ይችላል።

# በጤና አገልግሎት ውስጥ አስተርጓሚ ጥቅም ላይ አልዋለም የሚል ቅሬታ አሎት? ስለመብትዎ ጥያቄዎች አሉዎት?

**ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ያማክሩ:**
እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ ውስጥ የታካሚ እና የተጠቃሚ መብት ተወካይ
www.pasientogbrukerombudet.no ስልክ ቁጥር. 40 50 16 00

የእኩልነት እና የመድልዎ ጠባቂ ተወካይ, ስልክ ቁጥር. 23 15 73 00
LDO - Startside

ህዝባዊ አድሎኦን የሚከላከል ድርጅት (OMOD)
kontakt@omod.no og www.omod.no

እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ ውስጥ ያለ የኖርዌይ ጤና ባለስልጣን
Helsetilsynet fører tilsyn med barnevern, sosial- og helsetjenestene | Helsetilsynet ስልክ መቀበያ ስልክ ቁጥር: 21529900

**በአስተርጓሚው ጥራት እና ብቃት ላይ ቅሬታ አሎት?**
ቅሬታዎች እርስዎ ታካሚ ወደሆኑበት ተቋም ወይም ትርጉም በመንግስት ሴክተር ውስጥ (IMDi) ወደሚባለው የትርጉም ብሔራዊ ሙያዊ ባለስልጣን ወደሆነውን የውህደት እና የልዩነት ዳይሬክቶሬት (IMDi) መላክ ይችላሉ።

**ከተርጓሚዎች አጠቃቀም ጋር በተገናኘ በታካሚዎች መብቶች እና የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ህግ**
የታካሚ እና የተጠቃሚ መብቶች ህግ
Lov om pasient- og brukerrettigheter
(pasient- og brukerrettighetsloven) - Lovdata

**የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ህግ**
Lov om helsepersonell m.v. (helsepersonelloven) - Lovdata

**የትርጓሜ ህግ**
Lov om offentlige organers ansvar for bruk av tolk mv.
(tolkeloven) - Lovdata

**ይህ ድረ ገጽ በብዙ ቋንቋዎች የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ማውረድ ይችላሉ፦**
**www.helsenorge.no og www.helsedirektoratet.no**